**ለግንቦት 7 ንቅናቄ አመራርና ካድሬዎች! በተከታታይ ከማነሳቸዉ ጥያቄዎች የዛሬዉ፤**
**የወላስማ ዳውድ _ሚያዚያ 20 ቀን 2003 ዓ ም**

ደርግ ሊወድቅ አጥቢያ የብዙዎቻችን ዋነኛ ጭንቀት የነበረው ከመቀበር የማይድነውን መንግስት ፍጻሜ ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ተተኪው ለሕዝብ የሚበጅና በሕዝብ የሚዳኝ፣ የሀገራችንና የሕዝቧን አንድነት የሚያስከብር ስብስብ እንዲሆን ነበር። በወቅቱ ግን ለኢትዮጵያ ጥላቻ ያላቸው ሁሉ ወያኔን፣ ሽአቢያንና ኦነግን አቅፈዉና አግዘው ኢትዮጵያን ለሁለት ከፈሉ፤ አንድነትን ያስቀድማል የሚሉትን ክፍል መከራውን አሳዩት። መዘዙም እስካሁን የምናየው ነው። በዚያ ወቅት በአጭሩ የሚከተለው በገሃድ ታይቷል።

1. ዶክተር ብርሃኑ ነጋ  በአሜሪካ ከጓደኞቹ  ከእነ እንድርያስ እሸቴ *(በአሁኑ ሰዓት የመለሰ ዜናዊ የዲያስፖራ ጉዳይ አማካሪ ሚኒስቴር)* ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ስም ያለን ስብስብ አጣጥሎ ሆርን ኦፍ አፍሪካ የሚል ቡድን አቋቋመ (እስካሁን ኢትዮጵያ የሚል ስም አይመቸዉም)። ወያኔን፣ ሽአቢያንና ኦነግን አጅቦ አዲስ አበባ ገብቶ ከታምራት ላይኔ ጋር ስኳር ብጤ ቃመ፣ ላፍታ ያህል ታገት ቢደረግም እስካሁን በወያኔ ያልተወሰደ ንብረት አካበተ፤ ኋላም ታምራት ላይኔ "የትምክህትን ጎራ ለመናድ" አርባ የዩኒቨርስቲ መምህራንን ሲያባርር ከሆርን ኦፍ አፍሪካ ጓደኞቹ እንድርያስ እሸቴ፣ ሣሙዔል አሰፋና ሌሎቹ ጋር (ያዉም እርሱ ካለደሞዝ ላገልግል ብሎ) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዘዉ አለ፣ ተክለሰውነትም ገነባ።

2. አንዳርጋቸው ፅጌ በእንግሊዝ አገር ተከታታይ በራሪ ጹህፍ እያዘጋጀ ከያንግዜው በለንደን የወያኔ ተወካይ ከሚቹ አሰፉ ማሞ እና ከነዶክተር ከበደ ታደሰ እና ካሱ ኢላላ ጋር ሆኖ በኢትዮጵያ ስም ያለን ስብስብ ከልቡ ታገለ። ደርግም እንደወደቀ ወያኔን፣ ሽአቢያንና ኦነግን አጅቦ አዲስ አበባ ገባ። የአዲስ አበባ አስተዳደር ፀሐፊና የብአዴን ቁንጮ በመሆን በተለይ ትምክህተኛ የሚለውን አማራ ከሌሎቹ ጋር በመሆን ቁም ስቅሉን አሳየው። የሞተው ሞተ፣ የታሰረው ታሰረ፣ የተሰደደዉ ተሰደደ፣ ከፊሉም በማይፈወስ የሥነ አዕምሮ በሽታ እየተሰቃየ ነው። ወያኔም ገሸሽ እንዳደረገው የአማራው ትግል ከየት ወዴት የምትል መጽሀፍ በማሳተም ያንኑ የፈረደበትን አማራ ተሳለቀበት፣ ታሪኩንም አንሸዋሮ አቀረበ፣ ሌሎቻችንም በአማራዉ ላይ ጥላቻ እንድናሳድር የዘር መርዙን ረጨ።

የሚገርመው ግን አሁንም እኛኑ በመናቅ ሁለቱም ግለሰቦች ተመሳሳይ ድርጊት እየፈጸሙ ይገኛሉ። ያውም በኢትዮጵያ ስም የሚንቀሳቀስ ትብብርን እያፈራረሱ ***(እዚህ ላይ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በእሥር ቤት የቅንጅት መሪዮቻችንን በመከፋፈል፣ እነ ብርሃነ መዋ በአሜሪካ፣ አንዳርጋቸው ፅጌ በለንደን፣ ቅንጅትና ኅብረት አብረው መስራት የለባቸዉም የሚል የይፉ መመሪያ በመስጠትና በዉጭ ያለዉን ፀረ ወያኔ ትግል በማኮላሸት፣ ከተገንጣዮች ጋር ያልተሳካ ስብስብ መጀመራቸው ከማይረሱ እኩይ ተግባራቸዉ ውስጥ ዋነኞቹ ናቸዉ)***። ለዚህም አላማቸው፥ የታወቁ የደርግ ጊዜ ደም አፍሳሾቸን፣ ቀደም ሲል የወያኔ አገልጋይ የነበሩትንና አንዳንድ የእነርሱን ታሪክ የማያዉቁ የዋሃንን በመጠቀም፣ ሚዲያን በመቆጣጠር፣ መረጃ ከህዝቡ በመሰወርና በማዛባት፣ ነጭ ውሸት በመንዛት፣ ህዝቡን በዘር/በእድሜ/በሌላም በመከፋፈል፣ ጥቃቅን ልዩነቶችን እና ዘረኛነትን በማስፋፋትና በማራገብ ጭምር ነው።

የእኔ ጥያቄ ለግንቦት 7 ንቅናቄ አመራርና ካድሬዎች በአጭሩ ይህንን ታዉቁ ነበረ ወይ ነው? ካወቃችሁና የኢትዮጵያ ህልዉና አደጋ ላይ እንዳይወድቅ የምትፈልጉ ከሆነ ለምን አሁን ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈፀም ሁኔታዉን እያገዛችሁ እንደሆነ መልሱልኝ፤ ግልፅ መልስ እፈልጋለሁ፤ ጥያቄዎቼንም እቀጥላለሁ።

ኢትዮጵያ በንቁ ልጆቿ ጥበብ፣ በታጋይ ሕዝቧ ብርታት እና ከሁሉም በላይ በአላህ ኃይል ትጠበቃለች!!!